

# ክርስቶስ ብቻ

ብራና ሴሚናር 2016

## ወደ ተነሳንበት መመለስ

የተሐድሷዊያን ዐምስቱ “ብቻዎች”

ብራና
ሴሚናር
2016

ወደ ተነሣንበት መመለስ
የተሐድሷውያኑ ዐምስቱ “ብቻዎች”
ክርስቶስ ብቻ (Solas Christus)

# ክርስቶስ ብቻ (Solas Christus)



© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

# ታሳቁ ክፍፍል

## ፕሮቴስታንት

- *ሶላ ስክሪፕቱራ* - ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ
- ***ሶላ ክሪስተስ* - በክርስቶስ ብቻ**
- *ሶላ ፊዴ* - በእምነት ብቻ
- *ሶላ ግራቲያ* - በጸጋ ብቻ
- ሶሊ ዲኦ ግሎሪያ- ክብር ለኢግዚአብሔር ብቻ

## ካቶሊክ

- ቅዱሳት መጻሕፍት ሲደመር ትውፊት/ባህል
- **ክርስቶስ ሲደመር ቤተ ክርስቲያን**
- እምነት ሲደመር ሥራ
- ጸጋ ሲደመር መልካም ሥራ
- ክብር ለእግዚአብሔር ሲደመር ለሰው

## ክርስቶስ ብቻ



*መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ!* የፕሮቴስታንት አስተምህሮ ምንጭ ሲኾን፣ "መደበኛ መርሕ" ነው።

*ክርስቶስ ብቻ* የተሐድሶ አስተምህሮ ማዕከል ነው። ስለ ኢየሱስ ብቻ ነው!

ይህ የሆነው ለምንድን ነው?

1. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለእርሱ ከሚናገሩት የተነሣ፣ ማለትም ማንነቱ ስለ ሆነ

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

**ቈላስይስ 1 እና የክርስቶስ ማንነት**

“ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ” (ቁ. 3)

“የሚወድደው ልጁ” (ቁ. 13)

“የማይታየው አምላክ አምሳል” (ቁ. 15)

“ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር” (ቁ. 15)

“ርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በርሱ ነው” (ቁ. 17)

“አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው” (ቁ. 18)

“ርሱ የመጀመሪያ፣ ከሙታን መካከልም በኵር ነው” (ቁ. 18)

“በሁሉ ነገር ላይ የበላይነት ይኖረው ዘንድ” (ቁ. 18)

**ክርስቶስ ብቻ**

*መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ፦* የፕሮቴስታንት አስተምህሮ ምንጭ፣ “መደበኛ መርሕ” ነው።

*ክርስቶስ ብቻ፦* የተሓድሶ ነገረ መለኮት አስተምህሮ ነው። ስለ ኢየሱስ ብቻ።

ይህ ለምን ሆነ?

1. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ርሱ *ማንነት* ከሚናገሩት የተነሣ፤ ማለትም ስለ ማንነቱ ስለ ሆነ

ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ የከበረ ማንነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ማእከሉ ርሱ ነው።

በድጋሚ፣ ርሱ ለምን ማእከል ሆነ?

2. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ርሱ *ሥራ* ከሚናገረው ነገር የተነሣ፣ ማለትም ስለ ግብሩ/ሥራው

**ቈላስይስ 1 እና የክርስቶስ *ሥራ* (ግብረ ክርስቶስ)**

“በርሱም መዋጀትን በደሙ አግኝተናል፤ ይህም የኀጢአት ይቅርታ ነው።” (ቁ. 14፣ ኤፌሶን 1፥7ን ያመሳክሩ)

“ሁሉ ነገር በርሱ ተፈጥሯል፤ በሰማይና በምድር ያሉ” (ቁ. 16)

“በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ ሰላምን በማድረግ በምድርም ሆነ በሰማይ ያለውን ነገር ሁሉ በርሱ በኩል ከራሱ ጋራ አስታረቀ።” (ቁ. 20)

“ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለያችሁ በዐሳባችሁም ጠላቶች ነበራችሁ። አሁን ግን ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በርሱ ፊት ሊያቀርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ” (ቁ. 21-22)

“የዚህ ምስጢር ክብር ባለጠግነት በአሕዛብ መካከል ምን ያህል እንደ ሆነ ለማሳወቅ መረጠ፤ ርሱም የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ ነው።” (ቁ. 27)

*© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!*

**ክርስቶስ ብቻ**

*መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ፦* የፕሮቴስታንት አስተምህሮ ምንጭ፣ *"መደበኛ መርሕ"* ነው።

*ክርስቶስ ብቻ፦* የተሓድሶ ነገረ መለኮት አስተምህሮ ነው። ስለ ኢየሱስ ብቻ።

ለምን እንዲህ ሆነ?

1. ቅዱት መጻሕፍት ስለ ርሱ *ማንነት* ከሚናገሩት የተነሣ፤ ማለትም ስለ ማንነቱ ስለ ሆነ

ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ የከበረ ማንነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ማእከሉ ርሱ ነው።

በድጋሚ፣ ርሱ ለምን ማእከል ሆነ?

2. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ርሱ *ሥራ* ከሚናገረው ነገር የተነሣ፣ ማለትም ስለ ግብሩ/ *ሥራው*

ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ወሳኝ የሆነውን *ሥራ* አከናውኗል፣ ርሱ የድነት ማእከል ነው።

**ለምን ክርስቶስ ብቻ?**

ለመዳን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ *የግድ አስፈላጊ* ነው።

"በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐንስ 14፥6)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለድነት *በቂ* ነው

"እናንተም የገዥነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ *ሙሉ* ሆናችኋል" (ቈላስይስ 2፥10)

ስለዚህ፣ ድነት የሚገኘው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ *ብቻ* ነው።

ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና።" (የሐዋርያት *ሥራ* 4፥12)

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ለዚህ ጉዳይ አጽንዖት መስጠት ለምን አስፈለገ?




በዘመነ ተሓድሶ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ከፍ ያለ አመለካከት ነበራት።

የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት እውነታ በዓለም ዐቀፍ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች ላይ ተብራርቷል።

**የዓለም ዐቀፍ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች**

- ኒቅያ (325) - የክርስቶስን መለኮትነት አጽድቋል።

-ቊስጥንጥንያ (381) - የክርስቶስን ሰብእነት አጽድቋል

-ኤፌሶን (431) - ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት በአንድ ማንነት መሆኑን አጽድቋል።

-ኬልቄዶን (451) - የክርስቶስን ሁለት ባሕርያት፣ መለኮትና ትስብእት መሆኑን በድጋሚ አጽንቷል።

**ጉዳዩ**



ሐዳስያኑ በእነዚህ የእምነት አንቀጾች አስተምህሯዊ ይዘት ላይ ይስማማሉ።

የእነርሱ ጉዳይ ከክርስቶስ ይልቅ ሌሎችን *ተጨማሪዎችን* ከፍ ታደርግ ከነበረችው ከሮም ጋራ ነበር።

እነዚህ ነገሮች እነማን ነበሩ? (ማን ማን ናቸው?)

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ማርያም



- በድንግልና መፀነሷ
- አካላዊ ዕርገቷ (በአካል ማረጓ)
- ዘላለማዊ ድንግልና (ለዘላለም ድንግ
- የሰማይ ንግሥት
- የቤተ_ክርስቲያን እናት
- አማላጅ
- የምትመለክ (የአምልኮ ማእከል)

ጸጋን የተመላሽ ሆይ፤ ደስ ይበልሽ፤

እግዚአብሔር ካንቺ ጋራ ነውና፤

ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤

የማሕፀንሽም ፍሬ ኢየሱስ የተባረከ ነው።

ቅድስት ማርያም፣ የአምላክ እናት፣

አሁንም ሆነ በምንሞትበት ጊዜ፣

ለእኛ ለኀጢአተኞች ለምኚልን።

በአንቺ ጥበቃ ሥር ለመሆን ፈጥነን እንመጣለን፤

ቅድስት የአምላክ እናት፣

በሚያስፈልጉን ነገሮች፣

ልመናዎቻችንን አትናቂ፤

ነገር ግን ዘወትር ከክፉ አደጋ ታደጊን፤

የከበርሽና የተባረክሽ ድንግል ሆይ።

እመቤታችን፣ አማላጃችን፣ ጠበቃችን፣

ከልጅሽ አስታርቂን፤

ወደ ልጅሽ አቅርቢን፤

ስለ እኛ በልጅሽ ፊት ታዪልን።

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

**ማርያም አማላጅ ናትን?**

በፍጹም አይደለችም! አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ ርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው (1ጢሞቴዎስ 2፥5)

ማርያም ወልድ መለኮት የሆነውን ክርስቶስን እንድትወልድ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ሞገስ አግኝታለች። እውነትም ከሴቶች መካከል የተባረከች ናት (ሉቃስ 1፥42፡48)

ማርያም እግዚአብሔርን የምትፈራና በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ እምነት የነበራት ሴት ነበረች (ሉቃስ 1፥38፡45)

ይሁን እንጂ ኀጢአት አልባ አልነበረችም። *"መድኅኔቴ እግዚአብሔር"* በማለት ጸልያለች (ሉቃስ 1፥47)

ኢየሱስን ስትወልድ ድንግል የነበረች ቢሆንም ከዚያ በኋላ ግን ድንግል አልነበረችም (ማቴዎስ 1፥25፤ 13፥55-56)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድም ቦታ ወደ ርሷ የቀረበ ጸሎት የለም፤ ወደ ርሷ እንድንጸልይም አልተነገረንም።

**ጳጳሱ**



- የሮም ጳጳስ
- ቅዱስ አባት
- ታላቅ ሊቀ ጳጳስ
- በመንበረ ጴጥሮስ የሚቀመጥ የጴጥሮስ ተተኪ
- የክርስቶስ ወኪል
- እጅግ ቅዱስ ጌታ
- (የሚታይ) የቤተ ክርስቲያን ራስ
- የዓለማት ጌታ
- ኀጢአቶችን ይቅር የማለት ኀይል ያለው
- ከመንጽሔ ነፍስ (ነፍስ ከምትነጻበት) ስፍራ የማውጣት ኀይል ያለው
- በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው
- በክርስቲያኖች ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው
- በገዥዎች ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው
- አስተምህሯዊ መግለጫዎችን ሲናገር የማይሳሳት

"በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ለሮሙ ሊቀ ጳጳሳት ተገዥ ነው፤ እኛም ይህን እናውጃለን፤ እንናገራለን፤ እንገልጻለን፤ ለድነት ተፈላጊ መሆኑንም እንመሰክራለን። Boniface VIII, Unam Sanctam (1302)።

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ጵጵስናው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?

በፍጹም! ጴጥሮስ ከሐዋርያት የመጀመሪያው ነበር (ማቴዎስ 10፥2)፤ የሌሎቹ ሐዋርያት ቃል አቀባይ ነበር (ሐዋርያት ሥራ 2፥14)፤ ኢየሱስ ያቀርባቸው ከነበሩ ሦስት ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር (ማርቆስ 5፥37፣ 9፥2፣ 14፥33)።

ጌታውን በታማኝነት ያገለገለ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበረ (ዮሐንስ 21፥15-19)

ሆኖም ግን ተሳስቶ የነበረና ተግሣጽ የተሰጠው ሰው ነበረ (ገላትያ 2፥11-14)

የሮም ቤተ ክርስቲያን መሥራች አይደለም (በሮሜ መልእክት ውስጥ ስሙ አልተጠቀሰም)።

"ከእነርሱ ጋራ እኔም ሽማግሌ ... የሆንሁ" በማለት ራሱን ይጠራል (1ጴጥሮስ 5፥1) እንጂ ከዚህ በላቀ ሌላ ማዕርግ ራሱን አይገልጽም።

"ራሱን አጽናፈ ዓለማዊ ካህን ብሎ የሚጠራ ወይም ይህን ማዕርግ የሚሻ ሁሉ በትዕቢቱ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንገድ ጠራጊ ነው።" ጳጳስ ጎርጎርዮስ ቀዳማይ (ታላቁ) ከ. 540.

ጳጳስ = አባት። "በሰማይ ያለ አንድ አባት ስላላችሁ፣ በምድር ማንንም 'አባት' ብላችሁ አትጥሩ። መምህራችሁ አንዱ ክርስቶስ ስለ ሆነ፣ 'መምህር' ተብላችሁ አትጠሩ። ከመካከላችሁ ከሁላችሁ የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል፤ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል፤ ራሱን የሚያዋርድ ግን ይከበራል።" (ማቴዎስ 23፥9-12)

ጴጥሮስ ይህን ዘወትር በልቡ ያስብ ነበር። "ጴጥሮስም ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተቀበለው፤ እግሩም ላይ ወድቆ ሰገደለት። ጴጥሮስ ግን፣ 'እኔም እንደ አንተው ሰው ነኝና ተነሥ!' ብሎ አስነሣው።" (የሐዋርያት ሥራ 10፥25-26)።

ለጵጵስና ይሮጥ የነበረው ዲዮጥራጢስ እንጂ ጴጥሮስ አይደለም፤ "ነገር ግን መሪ መሆን የሚወድደው ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም" (3ዮሐንስ 9)።

### ቅዱሳን

- የሞቱ ክርስቲያኖች አሁን በሰማይ ናቸው።
- በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጠበቃ ተደርገው ይታያሉ።
- ልክ እንደ ማርያም፣ የአምልኮና የጸሎት ማእከል ናቸው።
- የቅዱሳን ግብር በጳጳሱ አማካይነት ለሌሎች ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።
- የቅዱሳን ምስል ያረፈበትን ነገር መያዝ በመንጽኤ
- ነፍስ የሚኖረው የቆይታ ጊዜ ሊቀንስ ይችላል።



© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ቅዱሳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሁሉም እውነተኛ ክርስቲያኖች፣ ሕያዋን ወይም የሞቱ ሁሉም ቅዱሳን ናቸው።

“በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ለመሆን ለተጠራችሁ በሮም ላላችሁ ሁሉ” (ሮሜ 1፥1)

የተቀደስነው በራሳችን የቅድስና ተግባር ሳይሆን በአዳኛችን ነው።

“በዚህ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ አማካይነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቀረበው መሥዋዕት ተቀድሰናል።” (ዕብራውያን 10፥10)

ቅዱሳን ተርፏቸው ለሌላው የሚሰጡት ይቅርና የራሳቸው የሆነ ግብረ ሠናይ የላቸውም።

“ስለዚህ እናንተም የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፣ ‘ከቍጥር የማንገባ አገልጋዮች ነን፤ ልናደርገው የሚገባንን ተግባር ፈጽመናል በሉ።’ ” (ሉቃስ 17፥10)

ርስ በራሳችን አንዳችን ለሌላችን ልንጸልይ እንችላለን፤ ለሙታን ግን ልንጸልይ አንችልም። ሳኦል ሳሙኤልን ከሞተ በኋላ በመፈለጉ ተኰንኗል (1ሳሙኤል 28፣ ኢሳይያስ 8፥19ን ያመሳክሩ)

## ክህነት



ለሮም ካቶሊካውያን ካህናት አማላጆች ናቸው።

በቅዱስ ሥርዐት ሹመት ከሌሎች ምእመናን የሚበልጡ ናቸው።

ኀጢአትን የማስተስረይ፣ ንስሓን የማዘዝና ሥርዐተ ቅዳሴን የመፈጸም ኀይል (ሥልጣን) ያገኛሉ።

ለመዳን፣ ኀጢአትን ለካህን መናዘዝ አስፈላጊ ነው።

Brana Gospel Focus Ministry
© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ካህናት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

በብሉይ ኪዳን፣ ክህነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሌዊ ነገድ ለሆኑት ለአሮን ዘሮች የተሰጠ ነበር። እነዚህ ካህናት የኀጢአት መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር።

አሁን በዐዲስ ኪዳን፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛው የኀጢአት ማስተስረያ ካህናችን ነው። ክህነቱ እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ሲሆን፣ መሥዋዕቱም ራሱ ነበር።

አማኞች ሁሉ ካህናት፣ ቅዱስና የንጉሥ ካህናት ናቸው። መሥዋዕቶቻችንም ስለ ኀጢአታችን የምናቀርባቸው ቁሳዊ ነገሮች ሳይሆኑ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚሆን መንፈሳዊ ነው።

መጋቢዎች ከሚመሯቸው ምእመናን በላይ የሆኑ ካህናት አይደሉም። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች የብሉይ ኪዳን ካህናት ያከናውኗቸው የነበሩ አንዳንድ ተግባራትን ያከናውናሉ፤ ለምሳሌ፦ ማስተማር፣ ማጽናናት፣ ምሳሌ በሚሆን ሕይወት መምራት።

**ሚልክያስ 2፥5-7**





“ከርሱ ጋራ የገባሁት ኪዳን የሕይወትና የሰላም ኪዳን ነበር፤ እነርሱንም ሰጠሁት፤ ይህም ክብርን አመጣ፤ ርሱም አከበረኝ፤ ስሜን በመፍራትም ጸና። እውነተኛ ትምህርት በአፉ ነበር፤ ምንም ዐይነት የሐሰት ነገር በአንደበቱ አልተገኘም፤ ከእኔ ጋራ በሰላምና በቅንነት ተራመደ፤ ብዙዎችንም ከኀጢአት መለሰ። ካህኑ የሁሉ ገዥ፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ስለ ሆነ፣ ከንፈሮቹ ዕውቀትን ሊጠብቁ፣ ሰዎችም ከአንደበቱ ትምህርትን ሊፈልጉ ይገባል፤”

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ቅዱሳት ሥርዐቶች



- ጥምቀት
- ማረጋገጫ / ማጽኛ
- ቊርባን
- ሹመት / ሢመት
- ጋብቻ
- ንስሓ
- ከፍተኛ ቅብዐ ቅዱስ

### ቅዱሳት ሥርዐቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ያሉት ቅዱሳት ሥርዐቶች ሁለት እንጂ ሰባት አይደሉም። እነርሱም ጥምቀትና የጌታ እራት ናቸው።

እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ወዲያውኑ በረከትን የሚሰጡ አይደሉም፤ ነገር ግን እውነተኛ እምነት ካለ በረከትን ያጐናጽፋሉ። እንደ ምልክቶችና ማኅተሞች ሆነው ያገለግላሉ።

እንደ ምልክቶች፣ ወደ እውነታው ይጠቊሙናል። እንደ ማኅተሞች ያረጋግጡልናል።

የውሃ ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ያመላክታል (የሐዋርያት ሥራ 11፥16)።

የጌታ እራት ኅብስትና ወይን የጌታን ሥጋ ደም ያመለክታሉ፣ ርሱን እንድናስታውስ ይረዳናል (1ቆሮንቶስ 11፥23-26)። ኅብስቱና ወይኑ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም አይለወጡም ወይም ርሱ እንደ መሥዋዕት ሆኖ አይቀርብም።

ቅዱሳት ሥርዐቶች ትልቅ ዋጋ ያለቸው ቢሆኑም፣ የግድ ግን አይደሉም። የሚያመለክቱት ይህን ነው።

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

**እነዚህ ሁሉ ጭማሪዎች ስሕተታቸው ምንድን ነው?**

**ሒሳብ ላይ እንዴት ናችኹ?**

ከዜሮ በታች ያሉ ቍጥሮች ላይ ከዜሮ በላይ የሆኑ ቍጥሮችን ብትደምሩ ምን ሊከሠት ይችላል።

ለምሳሌ፡- 10 + -20?

10 + -20 = - 10

ወይም 5 + -5?

5 + -5 = 0

ክርስቶስ + የሆነ ነገር = ምንም!




**እነዚህ ሁሉ ጭማሪዎች ምንድን ነው ስሕተታቸው?**

በእነዚህ ቍልፍ ጕዳዮች ላይ የሚደረግ ጭማሪ በርግጥ መቀነስ ነው።

ከዚህ ቀደም እንደ ተመለከትነው፣ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስን ባለሥልጣንነት ታረጋግጣለች፤ ነገር ግን በዚህም ላይ ትውፊትን ትጨምራለች።

በተግባር ሲታይ ይህ ማለት፣ መጽሐፍ ቅዱስ በትውፊት ታስሯል ማለት ነው (ማቴዎስ 15፥3-9)።

በተመሳሳይ መልኩ፣ ክርስቶስን ከሌሎች ነገሮች ጋራ ዐብሮ ከፍ ከፍ ማድረግ ክብሩን ማቃለል ነው።

አዳኝ ርሱ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ዐብሮ አዳኝ ነው ማለት ነው።

ርሱ አንድያ አማላጅ ሳይሆን የመጨረሻው አማላጅ ነው።

ርሱ ብቸኛው የቤተ ክርስቲያን ራስ ሳይሆን የማይታይ ራስ ነው።

የርሱ አስፈላጊ የመስቀል ላይ መሥዋዕት ነው፤ ይሁን እንጂ ኀጢአተኞችን ለማዳን በቂ አይደለም።

ከርሱ ጋራ አንድ መሆን በቂ አይደለም፤ ከሊቀ ጳጳሳቱም ጋራ አንድ መሆን ይገባል።

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ***የክርስቶስ ብቻ እውነታ***

ክርስቶስ ብቻ ቤዛችንና አዳኛችን ነው።

“በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከርሱ የተነሣ ነው፤ ርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኗል። እንግዲህ፣ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው፤ “የሚመካ በጌታ ይመካ።” 1ቆሮንቶስ 1፥30-31

ክርስቶስ ብቻ አማላጃችንንና ሊቀ ካህናታችን ነው።

“አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ ርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ።” 1ጢሞቴዎስ 2፥5-6

“ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።” ዕብራውያን 7፥25

ክርስቶስ ብቻ ንጉሣችንና ራሳችን ነው።

“እግዚአብሔርም ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ በቤተ ክርስቲያንም በማንኛውም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው። ርሷም ሁሉን ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው፣ የርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት።” ኤፌሶን 1፥22-23

መሥዋዕታችን ክርስቶስ ብቻ ነው።

“የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል።” 1ዮሐንስ 1፥7

“ምክንያቱም በአንዱ መሥዋዕት እነዚያን የሚቀደሱትን ለዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋል።” ዕብራውያን 10፥14

*© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!*




## ጆን ካልቪን ስለ *ክርስቶስ ብቻ*

ክርስቶስ ጣልቃ ገብቶ ቅጣቱን በራሱ ላይ ወሰደና፣ በኀጢአተኞች ላይ ይደርስ የነበረውን ፍርድ ተሸከመ። በገዛ ደሙ የእግዚአብሔር ጠላቶች እንዲሆኑ ያደረጓቸውን ኀጢአቶች ደመሰሰ። በዚህም አብን አስደሰተ… የአብን ፍቅርና መለኮታዊ ሞገስ ለማግኘት የምንመለከተው ክርስቶስን ብቻ ነው… ርሱ ኅሊናችንን ከኵነኔ ነጻ አድርጓልና "የሰላም ንጉሥ" (ኢሳይያስ 9፥6)፣ እንዲሁም "ሰላማችን" (ኤፌሶን 2፥14) ተብሎ ተጠርቷል። ይህን መንገዱን የምንጠይቅ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሠኘው መሥዋዕት በኩል መቅረብ አለብን። እግዚአብሔር፣ ቍጣውን ለማብረድ ኢየሱስ ባቀረበው አንድያ የስርየት መሥዋዕት ብቻ ደስ አይሠኝም ብሎ የሚያምን ሰው፣ አሁንም ከእግዚአብሔር ቍጣ በታች ነው። በዐጭሩ፣ ለራሳችን ሰላምን መፈለግ ያለብን በቤዛችን በክርስቶስ ሥቃይ ውስጥ ብቻ ነው። (Institutes of the Christian Religion 2.16.2)

### የሕይወት ተዛምዶዎች

ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ *ግልጽነት*

በማን በኩል ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንዳለብን አንጠራጠርም። መቼም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር የምንመጣው በልጁ በኩል ብቻ ነው "በርሱና በርሱ ላይ ባለን እምነት አማካይነት፣ በነጻነትና በልበ ሙሉነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን" (ኤፌሶን 3፥12)።

ከእግዚአብሔር *ጋራ* ባለን ግንኙነት - *ደኅንነት*

በውድ ልጁ በኩል እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዘላለማዊ ፍቅር ርግጠኞች መሆን እንችላለን። "ስለ ወደዳችሁኝና ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ ራሱ ይወድዳችኋል።" (ዮሐንስ 16፥27)

በክርስትና ሕይወታችን *ነጻነት*

የሰዎች *ሥርዐቶ*ችና አስተምህሮዎች ተገዢዎች አይደለንም። ጌታችን ክርስቶስ ብቻ ነው። ርሱን ለማገልገል ከሕግ ነጻ ወጥተናል። "ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድንኖር ነው። ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ ዳግመኛም በባርነት ቀንበር አትጠመዱ።" (ገላትያ 5፥1)

ከሌሎች አማኞች *ጋራ ኅብረት*

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

እኛ በዘር፣ በብሔር፣ በቤተ እምነት ወዘተርፈ የማንከፋፈል መንፈሳውያን ቤተ ሰቦች ነን።

“በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ።” (ገላትያ 3፥28)

በወንጌል ተልእኳችን *ፈጥኖ አብሣሪዎች*

ኀጢአተኞች ያለ አዳኝ ጠፍተዋል። ልንሰጣቸው የምንችለውን ነገር አጥብቀው ይፈልጋሉ። “ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ስለ ርሱስ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስማት ይችላሉ? (ሮሜ 10፥14)

*ዘላለማዊ ፍጻሜያችን* ከፊታችን ይጠብቀናል

የነገው መዳረሻችን ክብሩን እያየን ከክርስቶስ ጋራ በገነት መሆን ነው። “ይኸውም በሚመጣው ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ በቸርነቱ የገለጠልንን ወደር የሌለውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ነው፤” (ኤፌሶን 2፥7)

**ክርስቶስን መስበክ**



© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ የነገረ መለኮትና የድነት ማእከል ነው።

ይህም በመኾኑ፣ ሰባኪዎች እንደ መኾናችን ዘወትር ክርስቶስን መስበክ አለብን።

“በየዕለቱም፣ በቤተ መቅደስም ሆነ በየቤቱ፣ ኢየሱስ ርሱ ክርስቶስ መሆኑን ከማስተማርና ከመስበክ ከቶ ወደ ኋላ አላሉም ነበር።” (ሐዋርያት 5፥42)

“እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን ርሱን እንሰብካለን።” (ቈላስይስ 1፥28)

“እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንጂ ራሳችንን አይደለምና፤ እኛም ራሳችን ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ አገልጋዮች ሆነናል።” (2ቆሮንቶስ 4፥5)

**ይህን እንዴት ማድረግ እንችላለን?**



“ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ ምኵራብ ገባ፤ ሦስት ሰንበትም ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ፤ ክርስቶስ መከራን መቀበል እንዳለበትና ከሙታንም መነሣት እንደሚገባው እያስረዳ በማረጋገጥ፣ “ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ ርሱ ክርስቶስ ነው” አላቸው።” (የሐዋርያት ሥራ 17፥2-3)

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

**ጥያቄ፡- እዚህጋ "ቅዱሳት መጻሕፍት" የተባሉት ምንድን ናቸው?**






## የኤማሁስ መንገድ



"ርሱም እንዲህ አላቸው ... ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት

መጻሕፍት ስለ ርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው።"

(ሉቃስ 24፥27፡ 44-55ን ያመሳክሩ)

ልብ በሉ፡- ("በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሁሉ"

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስ በሁሉም ቦታ አለ!

በዐዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን፣ በብሉይ ኪዳንም ጭምር፣

"በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት" (ሉቃስ 24፥44)

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን



ትንቢቶች

ምሳሌ፣ ዘፍጥረት 3፥15

ዘዳግም 18፥15-19

ኢሳይያስ 7፥14፣ 9፥6-7፣ 42፣ 49፣ 50፣ 53

መዝሙራት 16፣ 22፣ 69፣ 110፣ 118

ዘካርያስ 6፥12-13፣ 9፥9፣ 12፥10

ታሪኮች

ምሳሌ፣ አብርሃም እና ይሥሐቅ (ዘፍጥረት 22)

ዮሴፍ እና ወንድሞቹ (ዘፍጥረት 37-50)

ዳዊት እና ጐልያድ (1ሳሙኤል 17)

ሙሴ እና እባቡ (ዘኁልቍ 21)

ዮናስ እና ዓሣው (ዮናስ 1 እና 2)

"ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳሉ ነበረ።" (ሮሜ 5፥14)

### ተምሳሌት

"አምሳል በቃል ያልተነገረ ትንቢት ሲሆን፣ ወደ ፊት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚታዩትን አንዳንድ ገጽታዎች አስቀድሞ የሚገልጽ በብሉይ ኪዳን ያለ ግለ ሰብን ወይም ኹነትን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃላዊ ያልሆኑ ትንበያዎች ልክ በቃል እንደ ተነገሩት ትንበያዎቹ ሁሉ እውነትና ጥልቅ ናቸው።" ጆን ማክአርቱር

"ተምሳሊት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን ንድፎች ወይም ሥርዐቶች ይተነትናል። እነዚህ ንድፎች ወይም ሥርዐቶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ በአንድ ኹነት፣ ግለ ሰብ ወይም ተቋም ውስጥ የሚታዩና ወደ ፊት በዐዲስ ኪዳን ትፍጽምታቸውን (ፍጻሜያቸውን) ያገኙ ናቸው። የቅዱሳት መጻሕፍት ሥርዐት ወይም ንድፍ ስለ ንጉሡና ስለ መንግሥቱ ያሉ እውነቶችን ያስተምራሉ።" ኒክ ሮአርኬ እና ሮበርት ክላይን

# የመከራና የክብር ሥርዐት



© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

## ኢየሱስ



“ክርስቶስ ይህን መከራ መቀበልና ወደ ክብሩም መግባት አይገባውምን?” (ሉቃስ 24፥26) ሥርዓቱ ለእኛም ተመሳሳይ ነው። “ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋራ ዐብረን ወራሾች ነን” (ሮሜ 8፥17)።

## ትግበራ (የሕይወት ተዛምዶ)



“መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ያመራሉ” እንደሚባለው፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም ሁሉ ወደ ክርስቶስ ይመራሉ። ስለዚህ ርሱን ከሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልንሰብከው እንችላለን፤ መስበክም አለብን።የብሉይ ኪዳን ታሪኮችን በተመለከተ፣ ታሪኮቹን ብቻ አትናገሩ! እነዚህ

ክፍለ ምንባባት ወደ ጌታ ኢየሱስ እንዴት ሊጠቍሙ እንደሚችሉ ዕሰቡ። ሕዝባችን በእጅጉ የሚያስፈልገው ጥሩ ጥሩ አርኢያዎችን መከተል ሳይሆን፣ የሚያምነው ታላቅ አዳኝ ነው።

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!

### መጻሕፍትን መመርመር



በእነርሱ የዘላለም ሕይወትን የምታገኙ እየመሰላችሁ፣ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፤ እነዚሁ መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው። (ዮሐንስ 5፥39)

“ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት

እየሰበከ፣ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ግልጽነት

ያስተምር ነበር።” (የሐዋርያት ሥራ 28፥31)

### አዳኙን መስበክ



“ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ፣ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ግልጽነት ያስተምር ነበር።” (ሐዋርያስ ሥራ 28፥31)

© Feb 2024 Brana Gospel Focus Ministry. Restoring the Gospel to pulpit!